የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ የካቲት ፲፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year No.21
ADDIS ABABA 22nd February, 2017

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩/፪ሺ፱ ዓ.ም

ለገርቢ ግድብ፣ የማሠራጫ መስመር እና የመጠጥ ውሃ ማዘጋጃ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከቻይና የኤክስፖርት - ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ……ገጽ ፱ሺ፭፻፵፫

**Content**

Proclamation No. 1001/2017

Export – Import Bank of China Loan Agreement for Addis Ababa Gerbi Dam Reservoir, Transmission Line and Treatment Project Ratification Proclamation. ……….. --Page 9543

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩/፪ሺ፱

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና የኤክስፖርት - ኢምፖርት ባንክ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማፅደቅ የወጣ አዋጅ

ለገርቢ ግድብ፣ የማሠራጫ መስመር እና የመጠጥ ውሃ ማዘጋጃ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ፱፻፳፫ ሚሊዮን ፯፻፲፪ ሺህ ፰፻ የቻይና ዩዋን (ዘጠኝ መቶ ሃያ ሦስት ሚሊዮን ሰባት መቶ አሥራ ሁለት ሺ ስምንት መቶ የቻይና ዩዋን) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና የኤክስፖርት - ኢምፖርት ባንክ መካከል እ.አ.አ. ዲሴምበር ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፮ በቤጂንግ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥር ፴ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION NO. 1001/2017

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE EXPORT – IMPORT BANK OF CHINA

**WHEREAS**, a Loan Agreement, between the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export –Import Bank of China stipulating that the Export-Import Bank of China provide to the Federal Democratic Republic of Ethiopia a loan in amount not exceeding 923,712,800.00 (Renminbi Nine hundred twenty three million seven hundred twelve thousand eight hundred Yuan only) for financing the Addis Ababa Gerbi Dam Reservoir, Transmission Line and Treatment Project was signed on the 27th day of December, 2016;

**WHEREAS**, the House of Peoples' representative of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 7th day of February, 2017;

**NOW, THEREFORE**, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "ለገርቢ ግድብ፣ የማሠራጫ መስመር እና የመጠጥ ውሃ ማዘጋጃ ፕሮጀክት ማስፈፀሚያ የሚውል ብድር ከቻይና የኤክስፖርት - ኢምፖርት ባንክ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩./፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. <u>የስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በቻይና የኤክስፖርት - ኢምፖርት ባንክ መካከል እ.አ.አ. ዲሴምበር ፳፯ ቀን ፪ሺ፲፯ በቤጂንግ የተፈረመው ቁጥር GCL No. (2016)19 Total No. (589) 1420303052016111861 የብድር ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫. <u>የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ሥልጣን</u>**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፱፻፳፫ ሚሊዮን ፯፻፲፪ ሺህ ፰፻ የቻይና ዩዋን (ዘጠኝ መቶ ሃያ ሦስት ሚሊዮን ሰባት መቶ አሥራ ሁለት ሺህ ስምንት መቶ የቻይና ዩዋን) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

***አዲስ አበባ የካቲት ፲፭ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም***

***ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ***

***የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት***

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may cited as the “Export – Import Bank of China Loan Agreement for Addis Ababa Gerbi Dam Reservoir, Transmission Line and Treatment Project Ratification Proclamation No.1001/2017”.

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Loan Agreement No.GCL No. (2016) 19 Total No. (589) 1420303052016111861 signed on the 27th day of December 2016 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Export – Import Bank of China is hereby ratified.

**3. <u>Power of the Ministry of Finance and Economic Cooperation</u>**

The Ministry of Finance and Economic Cooperation is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 923,712,800.00 (Renminbi Nine hundred twenty three million seven hundred twelve thousand eight hundred Yuan only) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall enter into force on the date of its publication on the federal Negarit Gazettee.

**Done at Addis Ababa, this 22nd Day of February, 2017.**

**Dr. MULATU TESHOME**

**PRESIDANT OF THE FEDERAL DEMOCRATICREPUBLIC OF ETHIOPIA**